# መታወቂያ?

ለመድነው ልበል?
        ረሀብተኛ መባሉን
የዓለምን ትዝብት፣ የዓለምን ምጽዋት
        በዝምታ መቀበሉን
ሆነብን ልበል?
        የወገን ሰቆቃ ዋይታ
የማያስደነግጥ የሩቅ ጩኸት
        የምናልፈው በዝምታ
ተቀበልነው ልበል?
        ረሀብ «ኖርማል» መሆኑን
የችጋር ዜና ስንሰማ
        ለጊዜው ብቻ ማዘኑን
ተቆራኘን ልበል?
        የቸልተኝነት ክፉ ሰይጣን
የንፋግነት ደዌ
        የተስፋ መቁረጥ እርግማን
አጸደቅን ማለት ነው?
        የረሀብ ቤተኝነቱን
የማንነታችን ምልክት
        መለዮ ሆኖ መቅረቱን?
ሠለጠንበት ልበል?
        በሚራብ ወገን መጨከኑን
የትውልድን ራዕይ ጨፍልቀን
        ተስፋውን፣ ሕልሙን ማምከኑን
ተቀበልነው ልበል?
        በወገን ስም መነገዱን
«አገሬ»፣ «ወገኔ» እያልን
        በባዶ ቃላት መሞላቱን
አወቅንለት ማለት ነው?
        ረሀብ ላይተወን መውደዱን
በዕንባና በደም
        ከእኛ ጋራ መዛመዱን
ተዋሃደን?
የሕጻናትን እልቂት ማየቱ
የወገንን ሲቃ፣ ጩኸት
        እንደ ሰርክ ዜና መስማቱ
ተላመድነው? ተቀበልነው?
        ለልመና መዳረጉን
ለኢትዮጵያ የተሰጠ ዕጣ ፈንታዋ መደረጉን
ለልጆቿ መደንገጉን
ድርቅ፣ ረሀብ፣ ልመና
        መታወቂያዋ መባሉን
እየተራቡ ተወልዶ
        እየተራቡ መሞቱን።
ተቀበልን ማለት ነው?
        የረሀብን ድል ነሺነት
ሕዝብ ማርገፉን ማስገበሩን
        የሀልውናውን ቋሚነት
ተሸነፍን ማለት ነው?
        በረሀብ ጦር ተወግተን
ስብእናችንን አስረክበን
        በደካማነታችን ተጠቅተን

ሰበረን ማለት ነው ረሀብ?
ዳግመኛ እንዳናንሰራራ
ባይተዋር፣ እርጉማን አድርጎን
መድቦን ከድውያን ተራ
ነጠፈች ማለት ነው ያቺ ምድር?
የአፍሪካ ተስፋ የነበረች
በልጆቿ ጩኸት ስቃይ
መሪር ሐዘን የደረበች
ውሃ ሞልቷት እንዳትጠጣው
ምግብ ሞልቷት እንዳትበላው
ነፍገናት፣ ከልክለናት
ተቆርቋሪ ዜጎች ላንሆን
ሙሉነቷን አጉድለን በክሕደት አምክነናት
ሥልጣንን ለጭካኔ፤ ፖለቲካን ለሌብነት
መከታ ጋሻ አድርገን ዘርፈንበት፣ ነጥቀንበት
መኖር መረጥን ማለት ነው?
የግፍ ሱሰኞች ሆነን
የሕዝብን እምነት አጉድለን
እስትንፋስ፣ ድምፁን አፍነን
ተዋዋልን ማለት ነው?
ረሀብ ላይተወን ላንተወው
ከራሳችን አልፎ፣ ተርፎ
ለመጪ ትውልድ ልናቆየው
እንደ ቅርስ ልናወርሰው
እንደ ቃልኪዳን ልንጠብቀው
ተስማማን?
ረሀብ እንዲያጠቃን
የእልቂት ግብዣው እንዳይበቃን . . .
ይኸው ነው ማለት ነው የእኛ ሕይወት?
ረሀብን ወርሰን ማውረስ
ለግል ኑሮ ብቻ ቋምጠን
የነገውን ተስፋ ማፍረስ
በቃ?!
ሀብት፣ ሥልጣን አግበስብሰን
ለራሳችን ብቻ ኖረን
በአስረሽ ምቺው ስካር
በምንቸገረኝነት ታውረን
በረሀብተኞች ዐፅም ላይ
በሰቆቃቸው ተረማምደን
በዕንባና በደማቸው
ልባችንን አደንድነን
በቃ?!
ይኸው ነው የእኛ ታሪክ?
የባዶነት ዘመን፣ የሃፍረት የውርደት ትቢያ
ለማስረከብ የቆረጥን
አንድነቷ የተናጋ፣ የተራቆተች ኢትዮጵያ
በቃ?!
ረሀብ ከእኛ ተዛመደ?
መጣ ሄደ መጣ ሄደ መጣ ሄደ
መጣ . . .
ተዋሃደን? . . . ተቀበልነው? . . . ተለመደ?
በቃ?!

---

ቴዎድሮስ አበበ
ስፕሪንግፊልድ፤ ቨርጂኒያ
June 18, 2008